# በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ስም ሽፋን ሕገ ወጥ አካሄድ

38ኛው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሕጋዊው ቅዱስ ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ በህመም ምክንያት ባልተገኙበትና ተወካይ ባልላኩበት እንደተካሄደና አወዛጋቢ ውሳኔዎች አስተላልፎ እንደተፈጸመ ይታወቃል። ይህ ሕጋዊውን ቅዱስ ፓትርያርክ ስልጣን የተጋፋው የሊቃነ ጳጳሳትና የካሕናት ጉባኤ በሰደት ላይ የሚገኘው ሲኖዶስ ሕልውና ያገኘበትን አብይ መርሕ የተጻረረ ነው። በዚህ ጉባኤ ላይ ከተላለፉት ውሳኔዎች መካከል አንዱ ሕጋዊው ቅዱስ ፓትርያርክ ለዋሽንግተን ዲሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የጻፉትን የፍርድ ቤት ድጋፍ ደብዳቤ ለመሻር የተደረገው ሙከራ ነበር። ሁለተኛው ደግሞ ዳላስ ኢየሱስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በህጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ጥላ ስር ለመታቀፍ ባቀረበው ጥያቄ ላይ የተደረገው ውይይትና ኦርቶዶክሳዊ ስርዓትን ያልተከተለው ምላሽ ነው።

የዲሲን ሀገረ ስብከት ጉዳይ አስመልክቶ ምንም እንኳን አንዳንድ አስተዋይ አባቶች ቅዱስ አባታችን በሌሉበት ማየት አንችልም ብለው ቢያሳስቡም ይህው ሀሳባቸው ተረግጦ ውይይት ከተደረገበት በኃላ የተደረሰበት ውሳኔ የቋሚ ሲኖዶስ አባላት ቅዱስ ፓትርያርኩ የጻፉትን ደብዳቤ እንዲያነሱ ካሉበት ቦታ ድረስ ሄደው እንዲጠይቁ ነበር። ይህ አልሆነም። ይልቁንም አሳፋሪውና አስገራሚው ክስተት ስብሰባው በተፈጸመ ማግስት በዲሲ ገብርኤል አውደ ምህረት ላይ ስለ “ቃለ ጉባኤው” የተሰጠው መግለጫ ነው። የቅዱስ ፓትርያርኩን ክብር እጅግ በመግፋት ፣ በማቃለልና በማንጓጠጥ መልክ “በማይረዱት ቋንቋ” የተጻፈ ነው በማለት የቅዱስ አባታችን ደብዳቤ በሊቀ ጳጳሳትና በካህናት ስብስብ እንደተሻረ በሃሰት ታውጇል። (ከዚህ መልዕክት ጋራ የተያያዘውን የድምጽ ፋይል ከታች ያዳምጡ)

ቅዱስ ፓትርያርኩን በአውደ ምህረት ሲዘልፍ የነበረው ግለሰብ ከሶስት ወር በፊት ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ የመጣ ሲሆን ስልጣነ ክህነቱም ከዲቁና ያላለፈ ነው። ይህ ግለሰብ በአገር ቤት በዘረኛው የወያኔ መንግስት ተልዕኮ በመንፈሳዊ ማህበራት ስርጎ በመግባት ተስፋ ተዋህዶ የሚባለውን የሰባክያን ማህበርና ሌሎችንም በመበተን የሚታወቅ ግለሰብ ነው። ከ20 ዓመታት በላይ በስደት ዓለም በህመምና በእንግልት ምዕመናንን በአንድነት በጸሎታቸውና በቡራኬያቸው ከተኩላ ሲታደጉ የቆዩትን ታላቅ አባት ባልተገራ አንደበት ማቃለሉ ያሳዝናል። ከሁሉም በላይ አሳዛኙ ደግሞ በቦታው የነበሩት የሜሪላንድና የአውስትራሊያ ሊቀ ጳጳሳት ሀሰተኛውን ዲያቆን ፍሬ ሰንበትን ለመግራትና ለማስተባበል አለመሞከራቸው ነው።

የዳላስ ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን የዕውቅና ጥያቄ አስመልክቶ በተደረገው ውይይት የዳላስ ቅዱስ ሚካኤል ዲያቆን አንዱዓለም እውቅና እንዳይሰጠው ሲሞግት ውሏል። በቤተ ክርስቲያን ያሉት አገልጋዮች የእምነት ችግር አለባቸው የሚል ማስረጃ የሌለው በግል ጥላቻ የተሞላ የሀሰት ክስ አቅርቧል። የዳላስ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በበኩላቸው አገልጋዩ ላይ ምንም ዓይነት የእምነት ችግር አለማየታችውን እንዲያውም ሙሉ የቤተክርስቲያን ልጅና አገልጋይ እንደሆነ መስክረው ቤተ ክርስቲያኑ እውቅና እንዲሰጠው አሳስበዋል። ብጹዕ አቡነ መልከጸዴቅም አንዱን የዳላስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንደሚያውቁትና በትምህርቱም ሆነ በስነ ምግባሩ አብረው ሲያገለግሉ ምንም ዓይነት ችግር እንዳላዩ መስክረዋል። በመጨረሻም ቤተክርስቲያኑ አገልግሎቱን እንዲቀጥልና የእምነት ችግር ለተባለው የካናዳው ሊቀ ካህናት እንዲጣራ በአስተያየት መልክ ቢያቀርቡም ክሱን የሚያጣራ አካል ሳይመደብ በአስተያየት መልክ ተወስዶ ነገሩ ታልፏል። በውሳኔው ያልተደሰተው አንድ እግሩን ከወያኔው ሲኖዶስ ጋር አንድ እግሩን ከስደተኛው ሲኖዶስ ጋር አድርጎ የሚጓዘው ከሳሹ ዲያቆን ፍጹም ስነ ምግባር በጎደለው፣ ስርአተ ቤተክርስቲያንን በጣሰና ያለችውን የሰንበት ትምህር ቤት ዲቁናውን በሚያሸር መልኩ ታላቁን ኦርቶዶክሳዊ ሊቅ የዳላስ የሐገረ ስብከትን ሊቀ ጳጳስ ተንጠራርቶ ዘልፏል። ስለ ዘለፋው እንኳን በቦታው የነበሩት አባቶች ሊገስጹት አልደፈሩም። እንዲህ ዓይነቱ አባቶችን በማሸማቀቅ ዝም እንዲሉ ማድረግ የማህበረ ቅዱሳን ዕኩይ የአስራር ስልት በህጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ውስጥም ሰርጎ እንደገባ ልብ ሊለን ይገባል።

የዳላስ ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን አሰመልክቶ የሊቀ ጳጳሳትና የካህናቱ ስብስብ የወሰነው ከላይ የተጠቀሰው ነው። ሆኖም ግን የስብሰባውን ውሳኔ የማይወክል ህገ ወጥ ደብዳቤ ጥያቄውን ላቀረቡት ባለጉዳዮች ወይንም ለሐገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሳይሆን ከሳሹ ዲያቆን ለሚያገለግልበት ደብር ለዳላስ ቅዱስ ሚካኤል ደርሶ የቅዱስ ሚካኤል ከብረ በዓል እለት ለህዝብ ተነቧል። ይሄው በብጹዕ አቡነ መልከጸዴቅ የተፈረመ አስገራሚ ደብዳቤ ስብሰባ ላይ የተወሰነውን ውሳኔ እጅግ የሚጻረር ነው። አባቶች ያቆዩልን ትልቅ ስርዓት፡- ማንንም ከመለየት በፊት ተከሳሹ ተጠርቶ መልስ እንዲሰጥ መጠየቁ ማብራሪያውም ባያረካ እንዲመለስ መለመኑ፣ ክርስቶስ የሞተላት አንዲት ነፍስ እንዳትጠፋ ጾም ጸሎት መያዙ፡- የት ቀረና ነው የከሳሽን ወሬ ብቻ በማድመጥ ሲኖዶስ ሳይመክርበት እንዲያውም ሐገረ ስብከቱ ባልሆነ ሊቀ ጳጳስ ብቻ ፍርድ የሚሰጠው? በሐገረ ስብከታቸው ጣልቃ የተገባባቸው ሊቀ ጳጳስ በግልባጭ እንኳን እንዲያውቁት አልተደረገም። በህጋዊው ሲኖዶስ ስም ህገ ወጥ አካሄድ ይሉሀል ይሄ ነው። የ90 ዓመቱን አዛውንት ታላቅ አባት አሳስቶ ይህንን ደብዳቤ ማን እንደ አጻፈው ለማወቅ የሮኬት ሳይንቲስት መሆን አያሻም። (ደብዳቤውን ከታች ይመልከቱ)

እንዲህ ዓይነት ሕገ ወጥ አካሄድ መላው ኦርቶዶካሳዊ ምዕመን  እጅግ ሊያሳስበው ይገባል። የዘረኛውን የወያኔን ስርዓትና የወያኔን ሲኖዶስ የተቃወምነው ከአባቶች ሥርዓት ፈቀቅ ብሎ መፈንቅለ ፓትርያርክ ስላደረገ  እንጂ የዓይናቸው ቀለም ስላላማረን እንዳይደለ ተገንዝበን  ይህ የበቀል ጦር በማን ላይ እንደተነጣጠረ መረዳት አለብን። እስከ አሁን ድረስ በአንድነት ቆመው ሕዝባቸውን በጸሎትና በእግዚአብሔር ቃል  አህጉራት እያቋረጡ የሚጠብቁትን ብርቅዬ አባቶችንና ህጋዊውን ሲኖዶስ ለመበታተን የተሸረበ ሴራ መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል። የእግዚአብሔር ቃል በ፲ኛ ጴጥሮስ ምዕ 5.8 “ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራል” እንዳለው ባላጋራችን ዲያቢሎስ ዛሬም በወያኔና መልዕክተኞቹ አድሮ በስደት ያለውን ኦርዶቶክሳዊ መንጋ ለመበተን እራስ የሆኑትን ቅዱስ ፓትርያርክ ፈልጎ ዳግም ጦር ሰብቆ በስደት ሀገር ሰርጎ ገብቶ እንደገና እያሳዳዳችው ይገኛል። አባቶችም ይህን በመገንዘብ አስፈላጊውን ጥንቃቄና ዝግጅት እንድታደርጉ ጥሪው ይድረሳችሁ። በቅርብ ያልመለሰ እረኛ ሲሮጥ ይውላል ነውና። የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች ይህንን ደባ ተከታትላችሁ በማጋለጥ ታሪካዊ ግዴታችሁን ልትወጡ ይገባል።

እግዚአብሔር አምላክ ረጅም እድሜና ጤና ለቅዱስ አባታችን ይስጥልን።

ወስበሐት ለእግዚአብሔር

ታዬ ብርሀኑ (taye_berhanu@ymail.com

ከላይ የተጠቀሱትን በዲሲ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምህረት ላይ በቅዱስ ፓትርያርኩ ላይ የተደረገውን ዘለፋና በዳላስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቹ ላይ የተጻፈውን ሕገ ወጥ  ደብዳቤ ከዚህ ጽሁፍ ጋር ተያይዟል።

